የረቡዕ ጥር 10 1998ዓም( ጃንዋሪ 18 2006)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## በአንድ ልሳን የማይናገር ሕዝብ የሚያጻምጠው አያገኝም

የሀገራችን ብሔራዊ ችግሮች የሁሉም ዜጋ የጋራ ጉዳይ መሆኑ ከታወቀ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም፥ የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ግን እስካሁን አልተቻለም። የሀገራችን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች ዓቢይና መሠረታዊ ምክንያት ያው ዞሮ ዞሮ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አለመስፈን መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም፥ ብሔራዊ ችግሮቻችን ግን፥ አምባገነን ሥርዓትን በማስወገድ ብቻ የሚያከትሙ አይሆኑም። እነርሱን ለማስወገድ ደግሞ ከአድማስ ባሻገር ማየትን፥ ብሔራዊ አጀንዳና ስትራተጂያዊ ወይም ዘላቂ ራዕይ መንደፍን ይጠይቃል። ይህም ከተሳካልን፥ አንድ ሌላ መሠረታዊና ዘላቂ የሆነ ተግባር ይጠብቀናል። እርሱም <u>ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ መኖሪያ</u> <u>ልትሆን የምትችልበትን ሥርዓተ-መንግሥት መመሥረት ነው።</u> የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ ዜጎቿ በሰላምና በነፃነት፥በአንድነትና በእኩልነት፥ በዕድገትና በብልፅግና የሚኖሩባት ሀገር አልሆነችም። ዛሬ፥ ሀገሪቱ፥ ዜጎቿና መንግሥት በአንድ አቅጣጫና ራዕይ የሚያማትሩ ሆነው አልተገኙም። በአንድ አቅጣጫና በአንድ ብሔራዊ ራዕይ ዙሪያ ካልተዋሀዱ በስተቀር፥ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት፥ሰፍኖ ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ይኬዳል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም። ለዚህ መደኅኒቱ ሁሉም ዜጋና ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፥ በጋራ መናገርና መሥራት ነው።ይህ ደግሞ ለጋራ ሀገር ጥቅም ከልብ ማሰብ ከተጀመረ ከባድ አይሆንም።

የተቃዋሚ ድርጅቶችና ሌሎቹም የኅብረት ሰብ ክፍሎች በዕርግጥ ይህችን ሀገር ከጠቅላላ ጥፋት ለማዳን ከፈለጉ፥ በሚከተሉት መሠረታዊና ብሔራዊ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ተስማምተው የጋራ የሆነ የተግባር አጀንዳ ነድፈው በጋራ መንቀሳቀስ መቻል አለባቸው። ይህ እስካሁን በሥራ ተተርጉሞ ታይቷል ለማለት አይቻልም። ሁሉንም በጋራ ሊያስተሳስሯቸውና የተባባረ ተግባር ሊፈፅሙ የሚያስችሏቸው መሠረታዊ ህቆች አሉ ብለን እናምናለን። እነርሱም:-

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ የማያወላውል አቋም መውሰድ፥ በጋራ መስማማት፥
- በህዝብ የእኩልነትና የዴሞከራሲ መብት ሙሉ በሙሉ መስማማት፤
- በሀገሪቱ የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ነፃነት ላይ ሁሉም ዕምነቱን ማስረገጥ፥
- በሀገሪቱ ዜጎች ዕኩልነትና ሉዓላዊነት፥ የህግ የበላይነትና የሀገሪቱን ሀብት ሁሉም ዜጋ በዕኩል የመጠቀም መብትና ነፃነት እንዳለው ማመን፥ መስማማት፥

- የሀገሪቱን የነፃነት ልዕልና፥ የዜጎቿን አንድነትም ሆነ ሰላምና መረጋጋትን አስገኝቶ፥ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ሊያመራ የሚያስችለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ብቻ መሆኑን አምኖና ተስማምቶ በጋራ መታገል፥ መሥራት፥
- ሁሉንም ያላሰተፈ፥ ያላካተተ፥ያላስተባበረ ትግል ግቡን እንደማይመታ በመረዳት፥ የጠነከረ ኅብረት ፈጥሮ የወያኔን ሥርዓት በጋራ ማስወገድ፥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እነኝህ ጉዳዮች የኢትዮጵያን ሕዝብና የተቃዋሚ ድርጅቶችን በአንድ ቃልና ልሳን እንዲናገሩ የሚያስችሏቸው ይሆናሉ ብለን እናምናለን። ዛሬ በብሔራዊ ጉዳይ ላይ ልብ ለልብ ተገናኝቶ ፥ ዐይን ለዐይን ተያይቶ፥ በአንድ ቃልና ልሳን መናገር ቢቻል ኖሮ፥ ትግሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግብን መትቶ ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ማምራት ይቻል ነበር ብንል፥ የቀቢፀ-ተስፋ አነጋገር ነው ልንባል አንችልም።

እስኪ ማንም ሳይጠይቀን፥ሳያሳስበንና ሳያስታውስን እራሳችንን ጠይቀን እኛው እራሳችን ለራሳችን መልስ እንፈልግ። እናምጣ። የአያሌ ምዕተ ዓመት ታሪክ፥ የበለፀገ ባኅል፥ ነፃነትና ማንነት ያለን ሕዝቦች፥ እንዴት ዛሬ በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ዋዜማ፥ ስለ ሀገር መኖርና አለመኖር፥ ስለ ዜግነታችን የማንነት ፍለጋ፥ በጋራ ሀገር በጋራ መኖር ወይም አለመኖር፥ ስለ ግዛት አንደነት መከበር/አለመከበር፥ ስለ ዜጎች የዜግነት ማንነትና ምንነት መጨነቅና መጠበብ እንገደድ? ስለ ኢትዮጵያ ብሔራዊና ስትራተጅያዊ ጥቅም ማሰብ እየቀረ፥ ስለ ጎጥና ቀበሌ መብተክተክ፥ ይገባን ነበር? ስለአንድነትና ኅብረት ቀርቶ፥ ስለ መለያየትና መበታተንስ መሳሳቡ አስፈላጊ ነው? እነኝህንና ለሌሎችንም ተመሳሳይ ዘመን-አመጣሽና ሰው -ሰራሽ ችግሮች፥ ጥያቄዎችና አሳሳቢ ጉዳዮች በአንድ ላይ መፍታትና ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት፥ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ተግባርና ኃላፊነት አይመስለንም። ይህ ብሔራዊ ጉዳይ ለአምባገነን መሪዎችና ነገ እንደጧት ጤዛ ለሚረግፉ ከፋፋዮችም የሚተው ነገር አይደለም። ወይም ደግሞ፥ ባዕዳን መፍትሄ እንዲያስገኙልን እነርሱኑ መለመን አይኖርብንም። የማንኛውም ሀገር ሕዝብ፥ የራሱን ችግር እራሱ መፍታት ካልቻለ፥ ብሔራዊ ነፃነቱን፥ ሰብዕናውንና ማንነቱ ሁልጊዜ በጥያቄው ውስጥ እንዳስገባ ይኖራል። እኛም የራሳችንን ችግር መፍታት ካልቻልን፥ ከዚህ ክስተት ልናመልጥ አንችልም። ተወደደም ተጠላ፥ እንደ ኮሶ መድኀኒት የሚመር፥ እንደ እንቆቆ የሚጎመዝዘውን ሀቅ አምነን መቀበል ይኖርብናል። ዛሬ:-

- የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የዜጎቿን አንድነትና ነፃነት የሚያጠፋ ቡድን በሥልጣን ላይ ቀጥሏል። መላው ሕዝብ ጠልቶትና ተቃውሞት፥ ንቆትና ደፍሮት በምርጫ ቢያስወግደውም፥በአሜሪካና በእንግሊዝ መንግሥታት ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር ብቻ ተቃዋሚዎቹን

እያጠፉ፥ እያሰረ እያሳደደና ሰላማዊውንም ሕዝብ፥ ህፃን፥ ሴትና ሽማግሌ ሳይቀር ባደባባይ እየጨፈጨፈ ይገኛል፡፡

- የኢትዮጵያ ሕዝብም በበኩሉ፥ አሰፈላጊውን መሥዋዕት በመክፈል የተቃውሞ ትግሉን በየአቅጣጫው ቀጥሏል፡፡ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ተማሪዎችም እንደጥንቱ እንደጧቱ የሕዝብ ወገንተኝነታቸውን ለማሳየት በመታገላቸው፥ በወያኔ ነፍሰ-ገዳይ ቡድኖች፥ እየተረሸኑ፥ እየታሰሩና እየተሰቃዩ ይገኛሉ፡፡ ወጣቱ ትውልድ ቆራጥ ትጋይነቱ በማስመስከር፥ ማነኛውንም መስዋዕት ለመክፈል መዘጋጀቱን በተግባር እያሳየ መጥቷል፡፡

- የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ተስፋ በሌለውና በማያንሰራራ ሁኔታ እየተንኮታኮተ ነው፡፡ የሥራ አጡን ቁጥር፥ በትክክለኛ አሀዝ መግለፅ የሚቻል አይደለም፡፡ የጎዳና ተዳዳሪው፥ የከተማ ነደያኑና ምፅዋተኛውን ብዛት ለተመለከተው ሀገሪቱን ያዝ ላታል እንጅ አያዝ ባትም፡፡ የኅሊና እስረኞችና የፖለቲካ መሪዎችን የወኅኒ ቤት ስቃይና መከራስ ምን ሊያውቀው ይችላል?

- ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከማነኛውም ዘመን ታሪኩ በበለጠ የተጠቃ፥ የተጨቆነ፥ የተበደለ ሆኗል፡፡

- በሌላ በኩል ግን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል፥ አልገዛም ባይነቱን በጋራ እየገለፀ በየአቅጣጫው እየተዋደቀ ይገኛል፡፡ በመላው ዓለም የሚኖረውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በበኩሉ፥ የዲፕሎማሲ ትግሉን በኅብረት እያጧጧፈው ይገኛል፡፡ ለሀገር ቤቱ ትግልም፥ የገንዘብ ፥ የቁሳቁስና ሌሎቹንም ዕርዳታዎች በማድረግ ላይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የሚያስደስተውና ለትግሉም ከፍተኛ አስተዋፅዖና ዕመርታ ሊሰጥ የሚችለው ደግሞ፥ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም እንደጥንቱ፥ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈልና በነመለስ ዜናዊ ከፋፋይ ወጥመድ ሳይገባ፥ ተባብሮ በአንድ ላይ ሀገሩን ለማዳን መነሳሳቱ ነው፡፡ ይህን የተባባረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የሚበግረው እንደማይኖር ጠላቱም ሆነ ወዳጁ ሊጠራጠር አይችልም፡፡ ይህን ሀቅ ተገንዝበው መለስ ዜናዊን የሚደግፉ መንግሥታት ፖሊሲያቸውን እንዲያስተካክሉ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ መጠየቁን ቀጥሏል፡፡

- የሰላማዊው ትግል ሂደት እየተሟጠጠ፥ የህጋዊው ተቃውሞና እንቅስቃሴ በሩ እየተዘጋ መምጣቱን ሁሉም ዜጋ ተረድቶታል፡፡ ስለሆነም፥ የትግሉ ሁለንተናዊ ገፅታና ዓይነት፥ ይዘትና አድማስ፥ ባኅርይና አቅጣጫ እየተለወጠ መምጣቱንና የኢትዮጵያ ሕዝብም ትኩረት ወደዚሁ የትግል ምዕራፍ እያነጣጠረ መሄዱንም ሁሉም የፖለቲካ ጠበብቶች ይስማሙበታል፡፡ የሀገሪቱ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን ማንም አይከራከርም፡፡

ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንደጥንቱ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸውን ከማንም አይጠይቁም፥ አይለምኑን፥ አይጠብቁምም:: ያስራ አራት ዓመታት የጥቃትና የሰቆቃ እሮሯቸውን ማንም አልሰማላቸውም:: በአንድ በኩል፥ የእነርሱን ጮኸትና አቤቱታ ሰማም አልሰማ፥ ዓለም፥ ምንም ለውጥ እንደማያስገኝላቸው ቢገነዘቡትም፥ በሌላ በኩል ግን እስካሁን ድረስ፥ በአንድ ልብ መገናኘት፥ በአንድ ቃልና ልሳን መናገር፥ አልተቻለም:: ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ መለወጥ ያለበት ይመስለናል:: የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ሁኔታ በመሠረታዊ መልኩ ለመለወጥና ብሎም ሀገሪቱን ከወያኔ የጎሳ አምባገነን አገዛዝ ለማዳን ከልብ ከታመነበት፥ የሚከተሉት ርምጃዎች በአፋጣኝ መከናወን ይኖርባቸዋል::

ሀ) ተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ በመቀመጥ፥ ያለባቸውን ችግር አስወግደው፥ አዲስ ኅብረት በመፍጠር፥ የጋራ ሀገራቸውን ለማዳን አዲስ የትግል ስልትና ስትራተጂ አውጥተው በጋራ መታገል አለባቸው:: ከተመክሮ መማር ቢጠቅምም ያለፈውን ድክመትና ስህተት ፤ፀገምና ዕፀፅ እያነሱ እየጣሉ ጊዜን ማጥፋት፥ መለስ ዜናዊን እንጂ ሌላ ማንንም አይጠቅምም:: ትግሉ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር ያለበት መሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወቅታዊ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን፥ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚያስገድዱት ዕውነታ ነው::

ለ) እስካሁን በጋር የትግሉ ሂደት ያልተካተቱ ድርጅቶችም ይሁን ስብስቦች በጋራ የትግሉ መድረክ መሳተፋቸው አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ወሳኝነትም ይኖረዋል::

ሐ) ሌሎች የኅብረትሰብ ክፍሎችና የብዙኃን ድርጅቶች፥ የሲቪክ ማኅበራት፥ ደራስያን፥ ጋዜጠኞች፥ ምሁራን፥ የሃይማኖት ተቋማት ወዘተ ሀገር በማዳኑ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉበት ተገቢ መድረክ ሊመቻችላቸው ያስፈልጋል:: ሁሉን ያላካተተ ሀገራዊ ትግል ግቡን ባፋጣኝ ሊመታ አይችልምናም ነው::

ኢትዮጵያን አሁን ከገባችበት አዝቀት ለማውጣት በአንድ የጋራ ዓላማ ስር ተሰባስቦ በጋራ ድምፅና ልሳን መናገር አማራጭ የለውም:: ስለዚህም ለወያኔ ጊዜ ሳንሰጥ በጋራ መክረን ተባብረን ለመታገል መጣር አለብን::